እምነትህን(ሽን) በስነጽሁፍ አማካኝነት የምታካፍልበት(ይበት) አንቂና (ተለዋዋጭ) መንገዶች።

እግዚአብሔር ታላቁን ተልዕኮ ሰጥቶናል።

“ለህዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል ከዚያም መጨረሻው ይመጣል” ማቴዎስ 24:14

እንዲህም አላቸው “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ” ማርቆስ 16፡15

ወንጌልን ለማካፈል እግዚአብሔር ከመረጣቸው ዘዴዎች አንዱ በታተመው ገጽ በኩል ነው።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በራሪ ወረቀቶችን ፣ መጽሄቶችን ወይንም መጽሀፍትን በማንበብ የወንጌል እና የመገለጥ(የጽኑ እምነት) እውቀታቸውን ይከተላሉ።

የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መስራቾች(ፋና ወጊዎች) እምነታቸውን ለማካፈል የታተመውን ገጽ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተጠቅመውበታል።

ጄምስ ዋይት አገልጋዮችን እንዲህ በማለት አሳስቧል

“ ህትመት ሃይለኛ ሞተር ነው። ስራውን ይስራና ሳንባዎችን ይታደግ(ይቆጥብ)፣ ዝግ ያለ መንፈስ ያለባቸው ንግግሮች እና መጻህፍት ሰሚውን ህዝብ እና የተናጋሪውን ሳንባ ከሚያደክሙ አጨቃጫቂና(አከራካሪ) ረጅም ንግግሮች አስር እጥፍ ውጤታማ ናቸው።

ወንድም ሆይ፣ ለሰዎች የበለጠ መልካም ነገር ልታደርግላቸው ትችላለህ፣ በመሆኑም አሁንም እንዲያነቡ በማድረግ ሳንባህንና እስትንፋስህን ትቆጥበዋለህ(አድን!) *James White, Review and Herald, December 18, 1856*

ኤለን ጂ ኋይት ስለ ስነ - ጽሁፍ ሃይልና አጠቃቀም ጽፋለች።

“የቤተክርስቲያን አባላት ሆይ ለስነ-ጽሁፎቻችን ስርጭርት ጠቀሜታ (ጠቃሚነት) ስትሉ ንቁ! እናም ለዚህ ስራ ብዙ ጊዜ ስጡ!” *Sothern Watchman, November20, 1902.*

ተስፋዎች

“ እግዚአብሔር ለኛ ታላላቅ ነገሮችን ያደርግልናል” በእግሩ ስር ትሁት እና አማኞች ሆነን ብንቆይ፣ በአብዛኛው የመጀመሪያ እምነታቸውን ህትመቶቻችንን በማንበብ ላይ የሚያደርጉ ከአንድ ሺህ በላይ ነፍሳት በፍጥነት ይለወጣሉ። *Review and Herald, November 10, 1885*

“ ጽሁፎቻችንን ለመሸጥ ወይንም ለመስጠት እናም በትህትና እውነትን ለማስተማር፣ በጎረቤቶቻችሁ ቤቶች ብትገቡ በእነዚህ ቤቶች ውስጥ በሚኖር በሰማይ ብርሃን ትታጀባላችሁ።” *Review and Herald, May 24, 1906.*

ተግዳሮት

“በደንብ ተጠናቅሮ የተዘጋጀ ጽሁፎችን በማሰራጨት ሊከናወን የሚችል ስራን አስመልክቶ እንደ ከዚህ ቀደሙ ተኝተናል”

ክርስቶስ በፍጥሞ ደሴት ለዮሐንስ የሰጠውን መልዕክት ዓለም እንዲያስተውለው በየጊዜው ጽሁፎችንና መጻሕፍትን በጥቡብ(በብልሃት) በመጠቀም አሁን ቃሉን በቆራጥነት እንሰብከው።
የክርስቶስን ስም የሚያውጅ ሰብአዊ ሰው ሁሉ “የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቧል አምላካችሁን ለመገናኘት ተዘጋጁ” በማለት ይመስክር። *9T,PP. 61, 62.*
ከሌላው የበለጠ አስፈላጊ የሆነ አንድ ሥራ ካለ ጽሑፎቻችንን ለሕዝብ በማቅረብ ቅዱሳን ጽሑፎችን እንዲመረምሩ መርዳት(መምራት) ነው። *The Colporteur Evangelist, P 80.*
“ህትመቶቻችን አሁን የወንጌል ዘር እየዘሩ ነው፣ በመሆኑም ብዙ ነፍሳትን ወደ ጌታ በማምጣት ረገድ ዓይነተኛ መሳሪያ(አጋዥ) ናቸው። ህትመቶቻችን በመሰራጨታቸው ምክንያት ሁሉም አብያተክርስቲያናት አንሰራርተዋል። በዚህ ስራ እያንዳንዱ የክርስቶስ ደቀመዝሙር የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይችላል።
Review and Herald, June 10,1880.

ስልጠና ያስፈልጋል (የሚያስፈልገው ስልጠና)

“ከእግዚአብሔር ጋር አብረን ሰራተኞች ነን (የስራ አጋሮች ነን)። ያለንበት ቦታ ምንም ይሁን ምን፣ - የኮንፍረንስ ፕሬዝዳንቶች፣ ሚኒስቴሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ተራ አባላት(ምዕመናን) ብንሆንም፣ ወቅታዊው እውነት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ለማብራት አብዛኛውን ዕድሎቻችንን በአግባቡ(በሚገባ) እንድንጠቀም በጌታ ዘንድ ተጠያቂዎች ነን። እንድንጠቀምባቸው እርሱ ከሾማቸው ዋነኞቹ ወኪሎች መካከል አንዱ የታተመው ገጽ ነው። በትምህርት ቤቶቻችን፣ በጤና ተቋሞቻችን፣ በቤተክርስቲያኖቻችን(በቤት ውስጥ የአምልኮ ቦታዎቻችን)፣ እናም በተለይ በዓመታዊ

የካምፕ ስብሰባዎቻችን ይህንን ውድ(የከበረ) ወኪል(ተቋም) በጥበብ መጠቀምን መማር አለብን። 9T, PP 86. 87.

ዘዴዎች

“የወንጌል ሰራተኞች ለሰዎች መጽሃፍ ቅዱስን እየከፈቱ ህትመቶችን(የታተሙ ጽሁፎችን) በማሰራጨት፣ ህይወታቸውን ስለባረከው ብርሃን በመናገር(በመተረክ፣) ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት ይሂዱ። በባቡሮች፣ በየጎዳናዎች፣ በባህር ላይ በሚጓዙ ትላልቅ መርከቦች እናም በደብዳቤዎች አማካኝነት በተገቢው መንገድ ጽሁፎች ይሰራጩ(ይበተኑ)”። 9T, p. 123.

“ብዙዎች በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ እስካሁን ድረስ ያለ ወንጌል መልዕክት ብርሃን ናቸው(የወንጌል መልዕክት ብርሃንን አጥተዋል)። አሁን የመጨረሻውን የማስጠንቀቂያ መልዕክት ድምጽ ለማሰማት ችላ የሚሉ ሁሉ የኋላ ኋላ (ለወደፊት) በጥልቅ ጸጸት ይሰቃያሉ። መልዕክቴ፣ ‘ማህበራት ወደ ከተሞች ለመግባት ይደራጁ ነው። ስብሰባዎችን ለማካሄድ አመቺ(ተገቢ) ቦታዎችን ፈልጉ። ጽሁፎችን አሰራጩ፣ ሰዎችን ለመድረስ ልባዊ ጥረቶችን አድርጉ” Evangelism, p. 96.

“በራሪ ወረቀቶች፣ ትራክቶች(ጽሁፎች)፣ ወረቀቶች እና መጽሐፎች በሁሉም አቅጣጫ(በየአቅጣጫው) ይሂዱ። በሄድከበት(ሸበት) ቦታ ሁሉ ባገኘኸው(ሸው) አጋጣሚ መስጠት ትችል(ችዪ) ዘንድ ተመርጠው የተሰደሩ ትራክቶችን(ጽሁፎችን) ከእናንት ጋር ያዙ። *Review and Herald, June 10, 1880.*

“እያንዳንዱ አማኝ ለዚህ ጊዜ የሚሆን መልዕክት የያዙ ትራክቶችን(ጽሁፎችን)፣ በራሪ ወረቀቶችን እናም መጽሐፎችን በሰፊው ያሰራጭ”። *Southern Watchman,* January 5, 1904.

“በልባቸው ለመስጠት ምክንያት ካላቸው(ፈቃደኛ ከሆኑ) ሰዎች ከተሰበሰበው ገንዘብ የተገኙ አራት፣ ስምንት ወይንም አስራ ስድስት ገጾች ካሏቸው ትናንሽ ትራክቶች በጥቂቱ ሊቀርቡ(ሊበረከቱ) ይችላሉ።

ለጓደኛዎ(ለወዳጅዎ) ሲጽፉ የፖስታ መላኪያ ሂሳብ ሳይጨምሩ አንድ ወይም ሁለት አያይዘ መላክ ይቻላል።

ለመስማት ጆሮውን(ዋን) ሊሰጥዎት ፈቃደኛ ለሚመስል በመኪናዎች፣ አልያም በጀልባ ውስጥ፣ ወይንም በመድረክ ላይ ላገኛችሁት ሰው ትራክት መስጠት ይቻላል”። 1T, pp. 551, 552.

“በህትመቶች ብቻ ሊደረሱ የሚችሉ ብዙ ቦታዎች አሉ፣ - መጽሐፍቶች፣ ወረቀቶች እናም ትራክቶች ሰዎች በሚያስፈልጓቸው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ተሞልተዋል።

ጽሁፎቻችን በየቦታው መሰራጨት አለባቸው ። ይኼኛው አልያም ያኛው፣ የትኛው እንደሚጸድቅ(እንደሚያፈራ) አናውቅምና እውነቱ በሁሉም ውሃዎች አቅራቢያ መዘራት አለበት። በተሳሳተ ፍረጃችን እውነቱን በቀላሉ ተዘጋጅተው ለሚቀበሉ ሰዎች ጽሁፎችን መስጠት ጥበብ የነደለው ነው ብለን ልናስብ እንችላለን። ወቅታዊዉን እውነት የያዘውን በራሪ ወረቀት የማደል(የመስጠት) መልካም ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል አናውቅም። *Christian Service. P. 15.*

ስነጽሑፍ እያንዳንዱ አባል ሊጠቀመው የሚችል መሳሪያ ነው።

ሁሉም ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዲያካፍሉ እና የቤተክርስቲያኒቷ የወንጌል ስራ አካል እንዲሆኑ ተጠርተዋል። ሁላችንም ተመሳሳይ ስጦታውች(መክሊቶች) የለንምና፣ ነገር ግን ሁላችንም ሁለት ነገሮችን ማድረግ እንችላለን።

- አንደኛ - መጸለይ። ሁሉም ክርስቲያን ለጠፉት እንዲጸልይ ተጠርቷል
- ሁለተኛ - ጽሁፎችን አጋራ(ሪ)። ቀላል ነውና።

ጽሁፎችን የማጋራት መርሆዎች

- መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ጸልዩ
- ግንኙነቶችን ይገንቡ - ሰዎች በጓደኛ የሚሰጣቸውን(የሚበረከትላቸውን) ጽሁፍ ለማንበብ የበለጠ እድል አላቸውና። እርስዎ እንዲስተናገዱ በሚፈልጉት መንገድ ሰዎችን ያስተናግዱ።
- አንድን የተለየ ቦታ ለመሸፈን ዕቅድ ያውጡና የመከታተያ ስልት ይንደፉ(ያዘጋጁ)።
- ሁልጊዜ የጽሁፍ አቅርቦቶችን ከእርሶ ጋር ይያዙ።
- ተስማሚ(ተገቢውን) ቁሳቁሶች ይምረጡ።
- ምን እንደሚል ያውቁ ዘንድ ጽሁፉን እራስዎ ያንብቡ።
- “ጠቃሚ ሆኖ አግኝቸዋለሁና ይህንን በማንበብ እንደሚደሰቱ አውቃለሁኝ(ተስፋ አለኝ)” ይበሉ።
- ጽሁፉን እንዲወስዱልዎት ሰውን በፍጹም አያስገድዱ።
- አይዝረከረኩ።

ጽሁፎችን ለመጠቀም መምረጥ

እያንዳንዱ ጽሁፍ የሚከተለው ሊኖረው ይገባል:

- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመዝገቢያ ካርድ፣ ወይንም መጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ለመጠየቅ መረጃ።
- ስልክ ቁጥር እና/ ወይንም ለተጨማሪ መረጃ አድራሻ።

ሁልጊዜ ከእርሶ ጋር የሚያዙ ዕቃዎች።

- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት አንድ
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመዝገቢያ ካርድ
- ትራክቶች
- ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ መንገድ

ስነጽሁፎችን ለመጠቀም የሚያመቹ ቦታዎች፣ ጊዜያቶች እና መንገዶች

በስራ ቦታ

- የንግድ ድርጅት ባለቤት ከሆኑ፣ ለደንበኞች፣ ለባለጉዳይ ወይንም ለታካሚዎች የጽሁፍ ማስቀመጫ(መደርደሪያ) ያዘጋጁ።
- በጠረጴዛዎት ላይ ትራክቶችን የያዘ የንግድ(የቢዝነስ ካርድ) መያዣ ያስቀምጡ።
- ለምሳሌ እንደ የጊዜው ምልክቶች(Signs of the Times)፣ የመልዕክት መጽሔቶች(Message Magazine)፣ ወይንም El Centinela መጽሄቶች አባልነት ተመዝግበው አባል በመሆን በመቆያ ቦታ ላይ ያስቀምጧቸው።

በእረፍት ጊዜ

- በአውሮፕላን ላይ በአጠገብዎ ለተቀመጠው ሰው ጽሁፎችን ያጋሩ።
- ትራክቶችንና የኪስ ጽሁፎችን/መጽሔቶችን በሆቴል ክፍሎች ውስጥ ይተዉ።
- በሆቴልዎ ክፍል ውስጥ በጌድዎን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ መዝሙረ ዳዊት 23 የመሳሰሉ ቦታዎች ላይ እንደ ምልክት ትራክቶችን ያስቀምጡ።
- ለሚያገኟቸው ሰዎች ጽሁፎችን ይስጡ።

በበዓላት ወቅት

የምስጋና መስጫ እራት ላይ፣ የልደት በዓላት ላይ፣ የገና መዝሙሮች ጊዜ። ምንም እንኳን የጅምላ ገንዘብ ማግኛ በዓላት(የበዓላት ንግድ) ወቅት ቢሆንም፣ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ለዓለም ስለአበረከተው ስጦታው አሁንም ልባቸው ይነካል። በዚህ ወቅት ከሌላው ጊዜ በበለጠ ሰዎች ለወንጌል መልዕክት ክፍት የመሆን ዕድላቸው ትልቅ ነው። ኤለን ጂ. ዋይት በዚህ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቤተክርስቲያን አባላት የታተመውን ገጽ(ጽሁፎችን) ለመመስከር እንዲጠቀሙበት አበረታታለች።

“የገና እና የአዲስ ዓመት ስጦታን ለወዳጆቻችን (ለጓደኞቻችን) የመስጠትን ልምድ ሙሉ በሙሉ አላወግዝም/አልኮንንም። በዚህ ውስጥ የቅርብ ወዳጆችን እግዚአብሔርን እስካልረሳን ድረስ(ካልረሳን)፣ እርስ በእርሳችን የፍቅርና የማስታወሻ ስጦታዎችን መለዋወጣችን ትክክል ነው። ስጦታዎቻችን ለተቀባያችን እውነተኛ ጥቅም እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባናል። የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ወይንም ለትዕዛዛቱ ፍቅራችን እንዲጨምር እንደነዚህ ያሉ መጻሕፍት እንደ አጋዥ እንዲሆኑ እመክራለሁኝ።” *Review and Herald, December 26,1882.*

በዓላትን ለምናውቃቸውና ለምንወዳቸው ሰዎች ወንጌልን ለማሰራጨት እንደ ጥሩ አጋጣሚ(ዕድል) ለመጠቀም እነዚህን ሐሳቦች ልብ ይበሉ።

- **በመስጠት የሚቀጥል ስጦታ።** የጊዜያቱ ምልክቶች (Signs of the Times) ወይንም፣ የመልዕክት መጽሄት (Message Magazine,) ወይንም El Centinela የሚባሉትን መጽሄቶች ለወዳጆችዎ፣ ለስራ ባልደረብዎ፣ ለዘመድ፣ ወይንም ለጎረቤቶች ይላኩ።
- **የየሱስ የውልደት ታሪክ** ከዘመናት ምኞት መጽሐፍ የብዙዎችን ልብ እንደሚነካ እሙን (እርግጥ) ነው።
- በእያንዳንዱ የገና ካርድ ውስጥ የኪስ ምልክቶችን ወይንም “*ከመጽሐፍ ቅዱስዎ ጋር ለጌድ ሰዓት ያሳልፉ*” የሚለውን ትራክት አብረው ጨምረው ይላኩ።
- በሁሉም የምስጋና መስጫ እና የገና ባስኬት/ቅርጫት ውስጥ በቤተክርስቲያኒቷ የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል በኩል ለቤተሰብ የሚሰጥ መጽሐፍ ይጨምሩ።

- **ነባር(የቀድሞ) እና አሁን በቤተክርስቲያን ውስጥ የማያገለግሉ አባላትን ያስታውሱ።**

  እንደናፈቃችኋቸውና ስለነሱ እያሰቡ እንደሆነ ይወቁ። መጽሐፍ ወይንም የመጽሔት መመዝገቢያ/አባልነት፣ ከገና ካርድ ጋር ወይንም ከቤተክርስቲያኗ ወይንም ከፓስተሩ ደብዳቤ ጋር አያይዘው ይላኩ።

- **የአካባቢዎን(የአገርኛውን) ጋዜጣ ይጠቀሙ።**
  በነጻ የመጽሐፍ አቅርቦት ማስታወቂያ ለመጠየቅ ለሚጽፍና ለሚደውል ለማንኛውም ሰው ያስቀምጡ።
- ቤተክርስቲያንዎ ለማህበረሰብ ልዩ የገና በዓል ዝግጅት ካላት እያንዳንዱ እንግዶችዎ ወደ ቤታቸው የሚወስዱት የመጽሐፍ ወይንም የመጽሔት ስጦታ መኖሩን ያረጋግጡ።

- በመቆያ ቦታዎ ውስጥ ወጣ ባለ በሚታይ ቦታ ላይ ተቀምጦ በአዳዲስ መጻህፍት የተሞላ መደርደሪያ ሁልጊዜ ለእንግዶች(ለጎብኚዎች) በረከት ነው። *"ነዳ ሁን፣ እራሰሀን እርዳ"* በሚለው ምልክት(አባባል) ጎብኚዎችን(እንግዶችን) ማበረታታዎትን እርግጠኛ ይሁኑ።

- በስብሰባ ጊዜ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመዝገቢያ ካርድ** እና ከርስቶስን ያማከለ ጽሁፍ ይተዉ።

- **ለጓደኛዎ(ለወዳጅዎ) መጽሐፍ ይስጡ/ይለግሱ።** ከአድቬንቲስት መጽሐፍት መደብርዎ/ማዕከልዎ የተገኘ መጽህፍ ፣ ከገበያ ለመግዛት(ለመገበያየት) ከከበደ መጽሐፍ ይልቅ፣ ለሚወዱት ሰው እጅግ በጣም ጥሩ(የላቀ) ስጦታ ነው።(ABC የስጦታ ካርድም መስጠት ይችላሉ)።

- **የሙዚቃ(የመዝሙር) ስጦታ ይስጡ።** የጸሎት ቤት ሙዚቃ(መዝሙር)፣በዓመት ወስጥ ለረጅም ሰዓታት ደስታን የሚያመጡ ሰፋ ያሉ የተለያዩ ዓይነት የድምጽ እና የመሳሪያ ቅላጼ ያላቸውን ዜማ ይሰጣል።

በእርስዎ የስም ዝርዝር ማህደር ውስጥ ልጅ አለ?

- መምህር ፣ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ፣ ወይንም የጎዳና ፈላጊ ክለብ መሪ ከሆኑ፣ ከእርስዎ የሚለገስ እንደ ትንሽ መጽሐፍ ስጦታ የልጅን ልብ የሚያስፈነድቅ ነገር የለም።

- ለጎረቤትዎ(ለወዳጅዎ) የበዓል ሰላምታዎችን በሚልኩበት ጊዜ ለልጆቻቸው ስጦታን መጨመርዎን አይርሱ። አዲሶቹ መጽሐፍ ቅዱስ ውድ ሀብት መጽሔቶች፣ ልጆች በሚገባቸው(በሚያስተውሉት) መንገድ የተጻፉ አስደሳች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በሚያጋሩ ታሪኮች የተሞሉ ናቸው።

በሰፈር ውስጥ

- **የእንኳን ደህና መጣችሁ ቅርጫቶች** - ለአዳዲስ ጎረቤቶችዎ ቅርጫት ይውሰዱና አንድ ዳቦ፣ ጭማቂ እና ጥሩ መጽሐፍ ወይንም መጽሄት ያካቱበት(ይጨምሩበት)።

- **ክልል(ቦታ) ይምረጡ** - በቤተክርስቲያን፣ በቤት አካባቢ ው.ዘ.ተ. እያንዳንዱን ቤት ይጎብኙ፣ እግረ መንገድዎን ጽሑፍ(መጽሐፍ) ይስጡ። መንፈስ እንደመራዎት (እንዳሳሰቦት) ከጎበኟቸው ጋር አብረው ይጸልዩ።

- **ስለ እምነታችን የሚናገሩ(የሚያወሱ) ጽሁፎችን ይስጡ።** በተገቢው መንገድ በቅደም ተከተል አስተካክለው(ሰድረው) በወር አንዴ ወይንም ሁለቴ ይስጡ። *"ምልክቶች - መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምልክቶች".....*የሚለው(የተሰኘውን) መጽሄት ለመጠቀም ጥሩ ስብስብ ነው ።

- **ለልጆች የሚሆን ቤተሰቦቻቸው(ወላጆቻቸው) ጋር የሚተው አንዳንድ ቁሳቁስ መኖሩን ያረጋግጡ።** *"የኛ ትንሹ ጓደኛ፣ የመጀመሪያው ሀብት፣ መመሪያ"* የተሰኙትን እና ትናንሽ የታሪክ መጽሐፍትን መጠቀም ይችላሉ።

- *የጊዜያቱ ምልክቶች(Signs of the Times), የመልዕክት መጽሄቶች (Message Magazines)፣* ወይንም *El Centinela* የተሰኙትን መጽሔቶች ለጎረቤትዎ ይላኩ።

የዕለት ተዕለት ዕድሎች

- ሁልጊዜ የተወሰኑ ጽሁፎችን ከእርስዎ ጋር ይያዙ። ጽሁፎችን ቶሎ ለማውጣት ሁልጊዜ ዝግጁ ሆነው ለመስጠት የሚያመችዎ የተለየ ቦታ ያስናዱ። ኪስ፣ የጓንት መያዣ፣ የእጅ ሻንጣ፣ ወይንም ቦርሳ ያዘጋጁ።

- **ትራክቶችን ለመጠቀም ስፍር ቁጥር የሌላቸው መንገዶች አሉ።**
- በመጠበቂያ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ
- ክፍያዎችን አብረው ያካቱ
- ለሚጎበኟቸው ሰዎች ይስጡ
- የሚስዮናውያን መጽሔት ለዶክተርዎ ቢሮ የሚሆን ወይንም በመጠባበቂያ ክፍል ውስጥ ይስጡ(ያስቀምጡ)።
- ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እየፈለጉ ከሆነ እና እምነትዎን ለማካፈል መንገድ እያዩ ከሆነ ትላልቅ መጻህፍትን ለመሸጥ ያስቡ።

ልዩ ዝግጅቶች

- በአካባቢዎ በሚገኙ ትርዒቶች ላይ ጽሁፎችን ያሰራጩ። በ 1940 ከሴንት ሉዊስ የዓለም ትርዒት በኋላ ኤለን ጎይት እንዲህ ብላ ጽፋለች:
- "ወደ መጨረሻው(ፍጻሜው) ስንቃረብ(እንደቀረብን መጠን)፣ በቅርብ ጊዜ በሴንት ሉዊስ እንደተደረገው ዓይነት ትርኢት፣ በከተሞቻችን ውስጥ ትላልቅ ስብሰባዎች እንደሚደረጉና እውነቱን በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ለማቅረብ ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅቶች መደረግ እንደሚገባቸው መመሪያ ተሰጥቶኛል።" ክርስቶስ በእዚህ ምድር በነበረበት ወቅት እንደነዚህ ያሉ

ዕድሎችን በደንብ ተጠቅሞባቸዋል። ለማንኛውም አላማ ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ በተሰበሰበበት በሁሉም ቦታ ላይ መልዕክቱን እያስተላለፈ ሳለ ድምጹ ጥርት ብሎ በጉልህ ይሰማ ነበር። በዚህም ምክንያት ከስቅለቱና ከእርገቱ በኋላ በአንድ ቀን በሺዎች የሚቆጠሩ ተለወጡ። በክርስቶስ የተዘራው ዘር በልቦች ውስጥ በጥልቀት ገብቶ በቀለ፣ እናም ደቀመዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በተቀበሉ ጊዜ መከሩ ወደ ውስጥ ተሰበሰበ.....

- “ልክ በሴንት ሉዊስ እንደቀረበው ትርዒት ዓይነት ሁሉንም ዕድል ማሻሻልና መጠቀም ይገባናል። በእንደዚህ ዓይነት ሁሉም ስብሰባዎች ላይ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ሰዎች ሊገኙ ይገባል። ልክ እንደ በልግ ቅጠሎች፣ የወቅቱን የእውነት ብርሀን የያዙ በራሪ ወረቀቶች በሰዎች መካከል ሊበተኑ ይገባል።
ለብዙዎች በዚህ ስብሰባ ለተገኙ፣ እነዚህ በራሪ ወረቀቶች ለህዝብ መፈወሻ እንደሚውል የህይወት ዛፍ ይሆኑላቸዋል።” *Letter 296, 1904 (Evangelism, p. 35).*

በቤተክርስቲያን ውስጥ

- **የጽሁፍ(የመጽሐፍ) መደርደሪያዎች በቤተክርስቲያንዎ ውስጥ**
በቤተክርስቲያንዎ ቅጥር ግቢ/መቆያ ስፍራ(ክፍል) ውስጥ በሚገኝ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ በቀላሉ ብድግ አድርገው ሊያነቧቸው የሚችሉ የንባብ ቁሳቁስ በማግኘታቸው የቤተክርስቲያን አባላት እና እንግዶች እንዲያነቡ ይበረታታሉ።

- **በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉ ስብሰባዎች** - በቤተክርስቲያን ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ስብሰባ በሚኖርዎት ጊዜ ሁሉ በነጻ የሚወሰዱ ጽሁፎች ያሉበት (የሚቀመጡባቸው) ጠረጴዛ እንደሚኖር እርግጠኛ ይሁኑ።

- **በቤተክርስቲያን ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር** - ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ወስጥ ወርሃዊ ወይንም የሩብ ዓመት ደብዳቤ ይላኩ። *ፖስታ መላኪያው፣ ደብዳቤ፣ እንዲሁም መጽሐፍ፣ የኪስ መጽሐፍ፣ ትራክት፣ ወይንም መጽሄት ማካተት አለበት።*

- **በቤተክርስቲያን ዙሪያ ያሉ ዚፕ ኮዶች፡** - ብዙ ጽሁፎች በቤተክርስቲያንዎ ዙሪያ ወደ ዚፕ ኮድ ወይንም ወደ *መጓጓዣ መስመር* ሊላኩ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል እንደ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ *መንገድ፣* Signs Specials

የተሰኘው መጽሄት። ይህንን በየዓመቱ ለብዙ ጊዜ ያድርጉ። እያንዳንዱ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመዝገቢያ ካርድ መያዙን ያረጋግጡ።

- **የሚሰዮናውያን መጽሔቶች፡** - የሚጸልዩላቸውን ግለሰቦችን ስም ይዘርዝሩ እናም ለእያንዳንዳቸው ከቤተክርስቲያኒቷ የሚሰዮናዊያን መጽሔቶች አንዱን ይላኩ። *ለምሳሌ የጊዜያቱ ምልክቶች፣ የመልዕክት መጽሔቶች፣ ኤል ሴንቲኔላ።*

- ከቤት ሳይወጡ ለረጅም ጊዜ ለቆዩ ሰዎች የተለያዩ ጽሁፎችን ለማጋራት የጉብኝት ፕሮግራም ያዘጋጁ።

- የቤተክርስቲያኒቷን ማስታወቂያ ይስጡ ወይንም መጽሐፍ ወይንም መጽሄት ያጋሩ።

- ዓይኖቹ የማንበብ ደስታን ላይፈቅዱለት የሚችልን ሰው መጽሐፍ ወይንም ታሪክ ያንብቡለት።

- **አዲስ አባልን ማቆየት(ማስቀረት)** - ከሚከተሉት ነገሮች ጥቂቶቹን በመጠቀም በቤተክርስቲያኒቷ ውስጥ ያሉ አዳዲስ አባላት እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው እርግጠኛ ይሁኑ።

- በጥምቀት ጊዜ የእርስዎ ክፍል(ቡድን) ለአዲስ አባል "የመንፈሳዊ ምግብ ቅርጫት" ሊሰጥ(ሊያቀርብ) ይችላል። ይህም የአምልኮ መጽሐፍ፣ የትንቢት መንፈስ መጽሐፍ፣ እና የታሪክ መጽሐፍን ሊያካትት ይችላል።

- በቤተክርስቲያኒቷ ውስጥ ለመጀመሪያው ዓመት በየወሩ ወይንም በየሩብ ዓመቱ ለሁሉም አዳዲስ አባላት መጽሐፍቶችን ይስጡ።

- **የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት** - በአጥቢያ ቤተክርስቲያንዎ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ አድቬንቲስት ካልሆኑ ቤተሰብ የመጡ የልጆች ወላጆች በየወሩ የሚሰዮናውያንን መጽሄት እየተቀበሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

- በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰላምታ ሰጪዎች(እንግዳ ተቀባዮች) እያንዳንዳቸው ለቤተክርስቲያኒቷ ጎብኚዎች(እንግዶች) የሚያካፍሉት የጽሁፍ አቅርቦት እንዳላቸው ያረጋግጡ።

የማህበረሰብ አገልግሎት

- **በማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል ውስጥ ያሉ የጽሁፍ መደርደሪያዎች** - በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል ጥሩ(በቂ) የስነ-ጽሁፍ አቅርቦት እንዳለው እርግጠኛ ይሁኑ።
- እያንዳንዱ የሚሰጥ የምግብና የልብስ ከረጢት መጽሐፍ ወይንም ትራክት መያዝ አለበት።

የወጣቶች ተሳትፎ

- የጎዳና ፈላጊዎች አባላትን በስነ-ጽሁፍ ማዳረስ ስራ ላይ እንዲሳተፉ ያድርጉ። ሊገኝ የሚችል የጎዳና ፈላጊዎች ክብር አለና።
- የጎዳና ፈላጊ አባላት የታሸጉ ሸቀጦችን በሃሎዊን ሲሰበስቡ፣ በእያንዳንዱ ቤት ጥቂት ጽሁፎችን እንደሚተዉ ያረጋግጡ።
- ትላልቅ መጽሐፍትን ለጎዳና ፈላጊዎች እና ለትምህርት ቤት ቡድኖች ገንዘብ ማሰባሰቢያዎች ይጠቀሟቸው።

የተለዩ ዕቅዶች(ስራዎች)

- **የሆስፒታል ጉብኝት** - "የወንጌልን ውድ እውነቶች የያዙ ህትመቶች ህመምተኞች(ታካሚዎች) በቀላሉ ማግኘት በሚችሉባቸው ክፍሎች ውስጥ መኖር አለባቸው።" *Evangelism, P. 96.*

- **የማረሚያ ቤት አገልግሎቶች** - በእስር ቤት አገልግሎት መርሃግብር(ፕሮግራም) ውስጥ ይሳተፉ።
  በንቃት ወደ ማረሚያ ቤት በመሄድ ቁሳቁሶችን ያጋሩ፣ ወይንም ወደ ማረሚያ ቤት ለታራሚዎች ይላኩ።
- ወርሃዊ የሚስዮኒያዊ መጽሄቶችን ለታራሚዎች ይላኩ።
- ለታራሚዎች የመጽሐፍ ቅዱስ የመላላክ(የተልዕኮ) ትምህርት ያዘጋጁ።
- ለማረሚያ ቤቱ ቤተ- መጻህፍት መጻሐፍትን ለማቅረብ፣ ከእስር ቤቱ ቄስ ጋር አብረው ይስሩ።

የባህር ማዶ ስራዎች(ዕቅዶች)

"ለባህር ማዶ የወንጌል ስራዎች መጎልበት የበለጠ ልበ ሰፊ፣ ራስን የመካድ፣ ራስን የመሠዋት መንፈስ ሲገለጽ የሀገር ውስጥ የሚስዮናዊነት ሥራ በሁሉም መንገድ እጅግ የላቀ ይሆናል፤ ምክንያቱም የሀገር ውስጥ የወንጌል ስራ ብልጽግና(መልካም ዕድል) በአብዛኛው የተመሰረተው በእግዚአብሔር አማካኝነት፣ ሩቅ በሆኑ አገሮች በሚደረገው

የወንጌል ሥራ አጸፋዊ ተጽዕኖ ላይ ነው። ነፍሳችንን ከኃይል ሁሉ ምንጭ ጋር የምናገናኘው ለእግዚአብሔር ጉዳይ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማቅረብ በንቃት (በትጋት) በመስራት ላይ ነው።" T6, P. 27.

- ***ሀይማኖታዊ(መንፈሳዊ) መጽሀፍትን እና መጽሄቶችን*** ከክፍል አባላቶች እና ቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉ ከሌሎች ሰዎች ይሰብስቡ። ወደ ሌላ ሀገር ለሚሰዮናዊ ስራ ወይንም ለቤተክርስቲያን ይላኩዋቸው። (መጽሄቶቹ የቤተክርስቲያን አባላት ስሞች እና አድራሻ ካላቸው ወደ ውጭ ሀገር ከመላክዎ በፊት አድራሻዎቹን ያስወግዱ። ይህ አባላትን ካልተፈለጉ የገንዘብ ጥያቄዎች ይጠብቃል።)
- በሰንበት ትምህርት ክፍልዎ ውስጥ የተሰበሰበውን ገንዘብ ይውሰዱና ወርሃዊ የሚሰዮናዊ የመጽሄት ምዝግባን ወደ ባህር ማዶ ቤተክርስቲያን ይላኩ።
- የእህትማማች ቤተክርስቲያን ህብረትን(ግንኙነትን) ባህር ማዶ ካለች ቤተክርስቲያን ጋር ያሳድጉ(ያጎልብቱ።)
- በተከታታይ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ውስጥ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጽሑፎችን ወደ ባህር ማዶ ይላኩ።
- ቁሳቁሶችን ወደ ውጭ ሀገር ለስነ - ጽሁፍ ወንጌላዊ ይላኩ።

ሌሎች ሀሳቦች

- የምልክቶች ዜና ሳጥን/Sign news box - ምልክቶች (Signs) መጽሄቶችን በከተማ ውስጥ ለሚገኝ የዜና ሳጥን ለማቅረብ(ለመስጠት) ቃል ይግቡ።
- በአካባቢዎ(በቀዬዎ) ጋዜጣ ላይ ትንሽ(ጥቂት) ማስታወቂያ ያስቀምጡ(ይለጥፉ)። ትንሽ መጽሐፍ ያቅርቡ(ይስጡ)። እንደ ሀዘን፣ ጋብቻ፣ የልጅ አስተዳደግን፣ ወይንም ጤናን ያሉ (የተመለከቱ/የመሳሰሉ)ጉዳዮችን የሚያወሱ ውድ ያልሆኑ ብዙ መጽሐፍት አሉ። በነጻ የሚሰጡ መጽሐፍትን የሚጽፉ(የሚደርሱ) ግለሰቦችን ብዛት ቢያዩ ይገረማሉ። እነዚህን መጽሐፍት ለሚጠይቁ ሰዎች ይላኩላቸው፣ በመቀጠል ከመጽሀፍቱ ጋር አብሮ የሚላክ የግል ማስታወሻ ይጻፉ። ለሚጽፉ ለእያንዳንዳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን ያቅርቡ(ይላኩ)።

- **የቦዘኑ(የማያገለግሉ/ከቤተክርስቲያን የጠፉ) የቀድሞ አባላትን ይድረሱ(ያግኙ)** - የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍልዎ በቤተክርስቲያንዎ የቀድሞ(የማያገለግሉ/ከቤተክርስቲያን የጠፉ) አባላትን ስም ዝርዝር ሰብስቦ መያዝ ይችላል። ለእነርሱ በመጸለይ ይጀምሩ። በመቀጠል፣ እንደ ምልክቶች(Signs) ወይንም መልዕክቶች(Messages) የመሳሰሉ መጽሄቶችን ይላኩ።

- **የመጽሐፍትን ሳጥን ያጋሩ** - የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍልዎ የመጽሀፍት መያዣ መግዛት ይችላል። ለክፍሉ አባላት ያከፋፍሏቸው፣ በመቀጠልም አባላት በቀጣይ ሳምንት ውስጥ እነዚህን መጻህፍት በማሰራጨት ረገድ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ይገዳደሯቸው። አንዳንድ የተጠቆሙ መጽሐፍት፦ ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ ወይንም የዓመቱ መጋሪያ መጽሐፍ።
  በቀጣዩ ሰንበት አባላት በሳምንቱ ውስጥ እግዚአብሔር ወደ ማን እንደመራቸው እና የነበራቸውን ተሞክሮ(ልምድ) እንዲናገሩ(እንዲያካፍሉ)ይፍቀዱላቸው።

- **መጽሐፍ ያጋሩ** - ብዙ የቡና መሸጫ ቤቶች/ቡና ቤቶች የመጽሐፍ ኪራይ/ብድር ክፍል አሏቸው። ሰዎች መጽሐፍ ይለዋወጣሉ። አንዱን ትተህ ሌላውን ትወስዳለህ። ይህ ጥሩ መጽሐፍ ለመውሰድ ትክክለኛው ቦታ ነው።

- **በቤተክርስቲያንዎ ወይንም በቤትዎ ሽያጭ አለ?** ነጻ መጽሐፍት ያለው(የያዘ) ጠረጴዛ ያካቱ። መልዕክት አዘል መጽሐፍትን አስቀምጠው ያጋሩ። ከቤተክርስቲያን አባላት ቀደም ብለው የተነበቡ መጽሐፍትን ይሰብስቡ፣ ከነዚህ መጽሐፍት ስንቶቹ እንደተወሰዱ ሲያዩ ይገረማሉ። ሰዎች "ነጻ" ይወዳሉና።
- ብዙ ጂሞች (የአካል ማሰልጠኛ) እና የአትሌቲክስ(የሩጫ) ክለቦች የመጽሄት መደርደሪያዎች አሏቸው። ሰዎች በስራ ላይ እያሉ ለማንበብ አንድ መጽሐፍ ትተው መጽሄቶችን ይወስዳሉ። የእርስዎን የጊዜያቱ ምልክት (Sign of the Times) መጽሄት ግልባጭ ይውሰዱና በመደርደሪያው ውስጥ ይተዉት።

የታተመው ገጽ ሀይል

"የደህንነት መልዕክት በታተመው ገጽ በኩል ሊቀርብ ይችላል። መቼም ወደ ኋላ አይሸሽም(አይገለበጥም፣) አይታክትም ፣ ፈጽሞ ተስፋ አይቆርጥም ፣ በምንተኛበት ጊዜ ይሠራል; በርካሽ ይጓዛል እና ምንም የሚከራይ ሕንፃ አያስፈልግም; ግለቱ ፈጽሞ አይጠፋም፣ እና ከሞትን ከረጅም ጊዜ በኋላ እንኳን ይሰራል። የታተመው ገጽ ወደ ቤት ውስጥ የሚገባና እዚያ የሚቆይ እንግዳ(ጎብኚ) ነው፤ እሱን በሚያነብበት ጊዜ ብቻ የሚያናግረው ስለሆነ፣ አንድን ሰው ሁልጊዜ በትክክለኛው ስሜት(ድባብ) ይይዛል። ሁልጊዜ ከተናገረው ነገር ጋር ይጣበቃል እናም መልስ አይሰጥም።"

"የታተመው ገጽ የማይሞት(ሞት አልባ) ነው። አንዱን ልታጠፋ ትችል ይሆናል፣ ነገር ግን ማተሚያ ቤት(ህትመት) ሚሊዮኖችን ማብዛት ይችላል። በሰማዕትነት በሞተ ቁጥር

ይነሳል(ያንሰራራል)። ለወንጌላዊው በተዘጉት በሮች በኩል ሊገባ ይችላል። በፋብሪካዎች፣ በባቡሮች፣ በኩሽና (በወጥቤት) ውስጥ ይሰብካል፤ ትምህርት ቤቱንና እስር ቤቱን ይጎበኛል፤ እየሞተ ባለ ሰው(በሟች) ጆሮ ውስጥ ያንሾካሹካል።

“የታተመው መልዕክት ሃይማኖቶቻቸው ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይሄዱ የሚከለክሏቸውን ሰዎች መድረስ ይችላል። በአዕምሮ የመረዳት(የማስተዋል) ችሎታው የሚኮራውን፣ ወንጌልን ለመስማት ወደሚቃወመው ወይም አብረውት የሚማሩትን ተማሪዎች ወይም ፕሮፌሰሮችን በመፍራት ከራሱ ጋር የሚያዛምደውን ተማሪ ሊደርስ ይችላል። ዓይንን ከመፈለግ ርቆ፣ ከመንግስት ጥልቅ ምርመራ ርቆ፣ ከአጉል(ከበዓድ) አምልኮ ጥያቄ ርቆ፣ ከጓደኞች(ከወዳጆች) እና ከቤተሰብ ወሳኝ ጣልቃ ገብነት ርቆ፣ የመዳን መልዕክት ሊነበብ እና ሊስተዋል ይችላል።”